# ይድረስ ለአዲስ ጉዳይ መፅሔት

# የሃሳብ ፍጭትን በመሸሽ ዜጎችን መፈረጅ ያሳፍራል

**መሐሪ ይፍጠር**

yiftermehari@gmail.com

**(ክፍል ሁለት)**

*በክፍል አንድ ፅሑፌ አዲስ ጉዳይ መፅሔት በአይጋ ፎረምና በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የወጣውን "ምን ዓይነት ሚዲያ ይበጀናል?" ለሚለው ፅሑፌ ምላሽ መስጠቴ ይታወሳል። ተከታዩ ደግሞ እነሆ።…*

*…ያም ሆነ ይህ ግን ምናልባት የፅሑፉ አዘጋጅ ከዲክሽነሪ ትርጉም ፈቺነት የዘለለ ዕውቀት ከሌላቸው፣ እኔ ስለ ልማታዊ ጋዜጠኝነት ሳወራ እርሳቸው ደግሞ የኒዮ-ሊበራሉን ቀኖና ያንበለበሉበትን አውድ ፈታ አድርጌ ባስረዳቸው ከፅድቅ እንጂ ከኩነኔ የሚያስቆጥርብኝ አይመስለኝም። ሰውዬው የቶማስ ጀፈርሰንን አተያይ አጥብቄ እንደተቸሁ እንዲሁም መፅሔታቸው ጀፈርሰንን የጠቀሰው 'ጋዜጣ ከሌለበት መንግስት ይልቅ መንግስት የሌለበትን ጋዜጣ እመርጣለሁ' የሚለውን የሚዲያን አስፈላጊነት ለመጥቀስ እንጂ የአሜሪካ ጋዜጠኝነት ወደ ኢትዮጵያ ይምጣ በሚል አይደለም ብለዋል። ታዲያ ይህን አባባላቸውን በሁለት መንገድ ማየት ይቻላል። ከተለመደው ውሸትና ስለ ፕሬስ ካላቸው ግንዛቤ።*

*በመጀመሪያ ደረጃ እኔ ከመፅሔቱ ላይ የጠቀስኩት የጀፈርሰንን ምናባዊ አፍቃሬ የጋዜጣ ዲስኩርን ብቻ አይደለም። ከአባባሉ ቀጥሎ መፅሔቱ በአቋም ደረጃ ያሰፈረውንም ጉዳይ ጭምር ነው። እርሱም "እውነትን ለማግኘት የሚረዳው ብቸኛውና ብልሃተኛው ፖሊሲ የሃሳቦችንና የመረጃውን ገበያ ያለመንግስት ጣልቃ ገብነት መተው ነው።… በኢትዮጵያ ያለው ተቃራኒ እውነታ ግን ጀፈርሰን መንግስታት እንዲኖራቸው ከሚያልመው ነጻ ፕሬስ የተለየ ነው…" እናም ፀሐፊው ሆን ብለው የዘለሉት ይህን ሃቅ ነው። በመሆኑም አንባቢያቸውንም ዋሽተዋል። ለነገሩ ይህ እኔ የጠቀስኩት አባባል ዕውን ፀሐፊ ተብዬው እንዳሉት ኢትዮጵያ ልክ እንደ አሜሪካ ዓይነት ፕሬስ ያስፈልጋታል ማለት አይደለምን?–ኧረ ለመሆኑ '…በኢትዮጵያ ያለው ተቃራኒ እውነታ ጀፈርሰን መንግስታት እንዲኖራቸው ከሚያልመው ነጻ ፕሬስ የተለየ ነው…' ማለት ከቶ ለእርሳቸው ምን ማለት ይሆን?...አሃ!...ሀገራችን የራሷን የሚዲያ ፍልስፍና ትከተል ማለት ነው እንዴ?...እናንተዬ ነገሩ እንዴት ነው!?...ግለሰቡ ከቀኝ ወደ ግራ በአማርኛ እየፃፉ፣ የገዛ ፅሑፋቸውን በአረብኛ ከግራ ወደ ቀኝ ነው እንዴ የሚተረጉሙት?...ምነው ጃል! ውሸትም ቢሆንኮ*

በድርበቡ ሲሆን ነው የሚያምረው…ጭልጥ አሉብኝሳ?…እኔም ሆንኩ አንባቢዎ በእርስዎ ቦታ ሆነን እንድናፍር ባያደርጉን ምናለበት?…ሌላው ቢቀር "መንግስት ሆይ፣ ሺህ ዓመት ንገስ" በሚለው ፅሑፍዎ ላይ የጀፈርሰንን ጉዳይ ካወጉበት ትንሽ ወረድ ብለው ከዕውነታው የራቀና ያለ አንዳች ምንጭ በደፈናው "መንግስት ከጊዜ ወደ ጊዜ በሚተገብራቸው የተለያዩ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጫናዎች እንዲሁም ግልፅ ማስፈራራቶችና እስከማሰር የደረሱ እርምጃዎች ሳቢያም የሀገሪቱ የፕሬስ ነፃነት ከጭላንጭል ብርሃን ወደ ድቅድቅ ጨለማ እየተሸጋገረ ነው" ያሉትስ የጀፈርሰናዊ እሳቤ እዚህ ሀገር ውስጥ መኖር አለበት ማለት አይደለምን?… ግና እዚህ ላይ በትክክል የተባለን ነገር ጠቅሶ ምላሽ መስጠት እንጂ ውሸትን ምን አመጣው?–እርግጥም ይህን የሚያውቁት እርስዎና የዝግጅት ክፍሉ ብቻ ናችሁ።

ለነገሩ እዚህ ሀገር ውስጥ ፕሬስ አራተኛው የመንግስት መዋቅር /The fourth Estate/ ሆኖ ሊሰራ አይችልም። ሚዲያ እንደማንኛውም የዴሞክራሲ ማጎልበቻ ተቋም የልማትና የዕድገት አጋዥነት ተግባሩን ብቻ ነው የሚወጣው። እርግጥ ምኞት ስለማይከለከል ጀፈርሰናዊ መሆንን መመኘት ይቻላል። መብትም ነው። ይሁንና ችግር የሚሆነው ከሀገሪቱ ተጨባጭ ነባራዊ ሁኔታ ውጪ የግድ የጀፈርሰን ዓይነት ሚዲያ እንከተል ሲባል ነው። መፅሔቱ በተደጋጋሚ በመንግስት ላይ ውርጅብኝ በማውረድ እየሻተ ያለው ይህን በመሆኑም እኔ በግሌ ልቀበለው አልችልም። ምንም እንኳን ሰውዬው በምላሻቸው ላይ ስለ ጉዳዩ ትንፍሽ ሊሉ ባይፈልጉም፣ በፅሑፌ ላይ ስለዚህ ጉዳይ በስፋት ገልጫለሁ–ሀገራችን የሚያስፈልጋት አሁን ያለውና ድህነት የተሰኘው ጠላቷን ድል ለማድረግ በምታናከውናቸው የልማትና የዕድገት የሞት ሽረት ጉዞዎች የሚደገፉት የልማት ጋዜጠኝነት ዘውግ መሆኑን በማስረገጥ። ከዚህ ውጪ የኒዮ-ሊበራል የሚዲያ አሰራርን በግድ እንከተል ማለት በፅሑፌ ላይ እንደጠቀስኩት 36 ቁጥርን ለሚጫማ ሰው 44 ቁጥር ጫማ የመግዛት ያህል ነው። ይህ ደግሞ ጫማው እንዲቆረጥ ስለሚያደርግ ተመራጭ አይደለም።..ለነገሩ የፀሐፊውና የእኔ ምልከታ የሁለት ዓለም ሙግት በመሆኑ በዚህ ጉዳይ ላይ ልንግባባ አንችልም። እርሳቸው ወይም መፅሔታቸው በልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ውስጥ ሆነው እየሰሩ የማያውቁትን የኒዮ-ሊበራል ሚዲያ አሰራርን ይናፍቃሉ፣ እኔ ደግሞ የሚዲያ አሰራር መወሰን ያለበት እንደየ ሀገሩ ተጨባጭ ሁኔታ እንጂ እንደ ቁሳቁስ ከውጭ እንደሚገባ ሸቀጥ መሆን የለበትም እላለሁ። የልማታዊ ጋዜጠኝነት አሰራር በአሁኑ ወቅት ለሀገራችን ፍቱን መድሃኒት መሆኑንም እናገራለሁ–ወፍ እንዳገሩ ይጮሃልና።

ሌላው እኔ ያላልኳቸውና በመፅሔቱ ግን ሆን ተብለው ተቀጣጥለው ከተሰፉት ጉዳዩች ውስጥ "ነፃ ሚዲያን ማን አቋቋማቸው? መንግስታት? እንደዚያ ከሆነስ ታዲያ ምኑን ነፃ ሆኑ?" የሚል አስገራሚ ሃሳብ ነው።…በመሰረቱ በፅሑፌ ውስጥ መንግስት ሚዲያን አቋቋመ አላልኩም። ፀሐፊው ናቸው የራሳቸውን የውሸት ዒላማ ለመምታት ሲሉ እንዲያ ያሉት። እንዲያም ሆኖ ግን መፅሔቱ

ከታች ወረድ ብሎ በአስገራሚና በጨቅላ የሚዲያ ትንታኔ ራሱ የፈጠረውን ጥያቄ መልሶ ራሱ ምላሽ ይሰጠዋል–"እንደኛ ሀገር ሁሉንም ነገር መንግስት የሚያቋቁም የመሰላቸው ፀሐፊው ጉዳዩ ተጣልዞባቸው ካልሆነ በቀር መንግስት ነፃ ፕሬስን ለማቋቋም ፈቃድ ስጥ ሲባል ይሰጥ ይሆናል እንጂ አስቦ የሚያቋቁማቸው አካሉ አይደሉም" በማለት። አባቴ ይሙት ድንቅ ትንታኔ ነው፣ሊቅነት እንጂ ጃል!።"እኔን ሊቅ ያርገኝ" አሉ ጎረቤታችን እማማ ስመኝ። እርግጥም ነፃ ፕሬስ የመንግስት አካል አለመሆኑን እንደ አዲስ የሚዲያ ግኝት ለአንባቢያቸው ያስተዋወቁትን እኚህን ሰው 'ሊቅ' ብላቸው የሚያንስባቸው አይመስለኝም።…እናንተዬ ማን ነበር አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል ያለው?–መቼም ስውሩ ፀሐፊ ሳይሆኑ ይቀራሉ?…

በመጀመሪያ ደረጃ እኔ በፅሑፌ ላይ ያሰፈርኩት አምባገነኑን የደርግ ስርዓት ታግሎ በመጣል ብሎም በህገ-መንግስቱ ላይ ሃሳብን ያለ ገደብ የመግለፅ መብትን በማስፈርና ተግባራዊ እንዲሆን በመፍቀድ "ለነፃው" ፕሬስ መፈጠር መንግስትም ሆነ ገዥው ፓርቲ ምክንያት ናቸው እንጂ፤ መፅሔቱ ለሴራ ትንታኔ ፍላጎቱ እንዳለው 'ነፃ ፕሬስን የሚያቋቁሙ መንግስታት ናቸው' የሚል ነገር አልወጣኝም። ይሁንና ፀሐፊው ለሀገራችን "ነፃ" ፕሬስ መፈጠር አሁን በስልጣን ላይ ያለው መንግስት አይደለም የሚሉ ከሆነ በጉዳዩ ዙሪያ በግልፅ መነጋገር ይቻላል–ምናልባትም ከሚዲያ አኳያ ያላቸው ዕውቀት 'ስለሚያስፈራ' 'ከደርግ ስርዓት ውድቀት በኋላ ለሀገራችን "ነፃ" ፕሬስ መፈጠርና በተቋምነት ደረጃ መቋቋም ብሎን መኀልበት እነ ጀፈርሰን ቁልፍ ሚና ነበራቸው' እንዳይሉኝ ስለምሰጋ ነው–መቼም "ያደቆነ ሰይጣን ሳያቀስ አይተውም" አይደል የሚባለው?…

ሌላው መፅሔቱ ወይም ፀሐፊው ከራሳቸው ፖለቲካዊ አጀንዳ ተነስተው 'ለህዝብ መስራት ማለት እንዴት የስርዓቱ ነፀብራቅ መሆን ማለት ነው ትላለህ? እኛ በሸያጭ ስለምንተዳደር ለህዝብ አንሰራም ወይ?፣ የህዝብ ወገንተኞች ኢ.ቴ.ቪ. እና አዲስ ዘመን ናቸው ብሎ ማውራትስ ጤነኝነት ነውን?' በማለት ራሳቸው የሚሰሩበትን ስርዓት በማጥላላት ብሎም እኔ የግሉ ፕሬስ 'አያስፈልግም' ሳልላቸው የተለመደውን ማጣፈጫ "ጨው" በመጨመር ሊሞግቱኝ ሞክረዋል። እርግጥም ማንም ሰው ያሻውን ሃሳብ መያዝ እንዳለበት ባምንም፤ የመፅሔቱ ሃሳብ ላዬ ላይ በግዳጅ ተጭኖ 'እንዴት እንዲህ ትላለህ?' የሚለውን 'የእኔን ብቻ ስማ ሙግትን' እንዲሁም 'ያልከው እንዲህ ስለሆነ ተቀበል' የሚልን ያልተገባ ትርጉም አዘል ሃሳብን ልቀበል አልችልም። መፅሔቱ በስርዓቱ ያለማመን መብት እንዳለው ሁሉ፤ እኔም የማምንበትን ማንኛውንም ሃሳብ የማራመድ ህገ-መንግስታዊ መብት አለኝ። እናም አሁንም ይሁን መቼም እኔ እስከማምነው ድረስ ለህዝብ መስራት ማለት የስርዓቱ ነፀብራቅ መሆን ማለት ነው– ለምን ቢባል፤ ስርዓቱን ያቋቋመው ህዝብ በመሆኑ ነው። ህዝብ ሃያል ነውና። ከዚህ አንጻር መፅሔቱ ሃቁን ገልብጦ እንደተረዳው ሳይሆን፤ ጉዳዩን ውድ አንባቢዎቼ በውል ተረድተውት የራሳቸውን ፍርድ ይሰጡ ዘንድ "ምን ዓይነት ሚዲያ ይበጀኛል?" በሚል ካቀረብኩት ፅሑፍ ዕውነታ ሰበዞችን መዝገቤ እንካችሁ ልበል።…

> *“…ማንኛውም ሚዲያ የተገነባበት ማህበራዊ-ኢኮኖሚ አውድ (Socio-Economic Context) ነፀብራቅ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። እናም በሀገራችን ውስጥ እየተገነባ ያለውን ስርዓት ቅጥ ባለው መንገድ መረዳት ተገቢ ነው። አሁን እየተገነባ ያለው ስርዓት ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ እንጂ፤ ሊበራሊዝም አይደለም። ስለሆነም መፅሔቱም ሆኑ ሌሎች የሃሳቡ አራማጆች እርግጥም ለህዝብ እናስባለን የሚሉ ከሆነ መሆን የሚገባቸው የስርዓቱ ነፀብራቅ ነው። በሊብራሊዝም ስርዓት ውስጥ ልማታዊ አስተሳሰብ ያለው ፕሬስ እንደማይገነባ ወይም ቢገነባም ጠብ የሚል ነገር እንደማያመጣ ሁሉ፤ በልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ውስጥም የሊበራሊዝም አቀንቃኝ የሆነ ሚዲያ ቢገነባ ምናልባትም ከአደናቃፊነት የዘለለ ሌላ ፋይዳ ላይኖረው ይችላል። ይህ ማለት ግን በሀገራችን ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ውስጥ የግል ሚዲያዎች አያስፈልጉም እያልኩ እንዳልሆነ ሊታወቅልኝ ይገባል። ይልቁንም የግሉ ፕሬስ ከፍፁም ጥላቻና ፅንፈኝነት እንዲሁም ህገ-ወጥ ከሆነ ጥቅም ናፋቂነት ተላቅቆ ሀገራዊ በሆነ መንገድ ተግባሩን ካከናወነ፤ በመካሄድ ላይ ላለው የሠላም፣ የልማትና የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ባህል ግንባታ ስር መስደድ የበኩሉን ጠጠር ሊወረውር መቻሉ አያጠራጥርም።”* … እንግዲህ ውድ አንባቢያን ሆይ! በፅሑፌ ላይ ያሰፈርኩት ሃቅ ይኸው ነውና ፍርዱን ለእናንተ እተወዋለሁ።…

ያም ሆነ ይህ እስቲ ወደሌላኛው የመፅሔቱ ድርሰት እንመለስ። መፅሔቱ ‘ፀሐፊው የአዲስ ጉዳይ የገቢ ምንጭ ግንቦት ሰባት፣ ፅንፈኛው ዲያስፖራ ምናምን ነው አሉ’ ባይ ነው። ለነገሩ እኔ ሃቁን አውቄው ብፅፍ ደስ ባለኝ ነበር። ግና መፅሔቱ የማን እንደሆነ ስለማላውቅ እንዲህ የሚል በማስረጃ ያለተደገፈ ነገርን አልፃፍኩም–እኔ የመፅሔቱን ፀሐፊ አይደለሁምና። እናም የእኔ አባባል የተመሰረተው በዓለም ላይ የሚገኝ ማንኛውም ሚዲያ ርዕዮተ-ዓለማዊ ዝማሜው ከገንዘብ ምንጩ ጋር እንደሚያያዝ ጥቅል ግንዛቤን መፍጠር ከመሆኑም በላይ፤ አንዳንድ የሀገራችን ሚዲያዎች ግን የተቃዋሚዎችንና የፅንፈኛ ዲያስፖራዎችን እንዲሁም የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በአሸባሪነት የፈረጃቸውን ድርጅቶችን አጀንዳዎች በቅብብሎሽ መልክ ሲያራግቡ መመልከት የተለመደ ሆኗል በሚል ነው። እስቲ በዚህም ላይ ያልኩትን ለውድ አንባቢዎቼ ከፅሑፌ በመጥቀስ ላስረዳ።

> *“…በአይጋ ፎረም ድረ-ገፅ ላይ “አዲስ ወይስ አሮጌ ጉዳይ?” በሚል ርዕስ የተፃፈን አስተያየት አነበብኩ። ፅሑፉ “አዲስ ጉዳይ” የተሰኘው የግል መፅሔት በአንድ ጊዜ ዕትሙ ብቻ ያቀረባቸውን ሚዛናዊነት የጎደላቸውንና ከነባራዊው ዕውነታ ያፈነገጡ እንዲሁም የጋዜጠኝነት ስነ-ምግባርን ያልተከተሉ ዘገባዎችን በመሔስ ላይ ነበር ያጠነጠነው። በወቅቱ እኔም እንደ አንባቢ*

*የሀገራችን የግል ሚዲያዎች ለዴሞክራሲ ባህል ግንባታችን የበኩላቸውን እገዛ እንደሚያደርጉ የማምንበት ቢሆንም፤ እዚህ ሀገር ውስጥ ምንም ነገር ያልተሰራ ይመስል ሁሌም መንግስትን በማውገዝና በማብጠልጠል፣ ከፍ ሲልም የራሳቸውንና የፅንፈኛ ዲያስፖራውን አቋም በማከል እንዲሁም ከሙያው ስነ-ምግባር ውጪ በሆነ መልኩ እንደ ግንቦት ሰባት ዓይነት ባንዳ ፖለቲከኞችን አጀንዳ እየራቡ እንደምን ዴሞክራሲያችንን ሊያጎለብቱ ይችላሉ? የሚል ጥያቄ በውስጤ ማጫሩ ግን አልቀረም።…’* ታዲያ ከዚህ ፅሑፌ ማንኛውም አንባቢ እንደሚረዳው በውጭና በውስጥ ሃይሎች አማካኝነት የአጀንዳ ቅብብሎሽ እንደሚካሄድ እንጂ፤ ፀሐፊው አጣመው እንደተረጎሙት የመፅሔቱ የገቢ ምንጭ  ግንቦት ሰባትና ፅንፈኛው ዲያስፖራ ነው የሚል አይደለም። እኔ ያቀረብኩት ስለ አጀንዳ ቅብብሎሽ እንጂ ስለ ሚዲያ የገንዘብ ምንጭ ዝውውር አይደለም። እናም ይህን የፈጠረው የፀሐፊው ምናባዊ እሳቤ ሊያም ምናልባትም እርሳቸውና እርሳቸው ብቻ የሚያውቁት ጉዳይ ሊሆን ይችላል።

ዳሩ ግን አሁንም ቢሆን እምነቴን ከመግለፅ ወደ ኋላ አልልም። እንደሚታወቀው በተለያዩ ወቅቶች ግንባር ሆነናል ብለው እንደ በሬ እርስ በርሳቸው የሚጋጩት እነ መድረክ እንደ አንድ ጨለምተኛ ተቃዋሚ ፓርቲ በሀገር ውስጥ የሚያነሱትን የፕሬስና ሌሎች ተዛማጅ የበሬ ወለደ ዲስኩሮችን መፅሔቱ በተመሳሳይ መንገድ ‘በዐብይ ጉዳይ’ አምዱ ላይ በፊቃደኝነት የተባለውን አሉባልታ እየተነተነ ሲያራግብ እንደነበር እንኳንስ ፀሐፊው ቀርቶ እኛ አንባቢዎቹም ብንሆን የምንዘነጋው ሃቅ አይደለም። በተለይም ከመሰንበቻው የያኔው ኢትኦጵ ጋዜጣ አዘጋጅ የነበረውና የዛሬው የግንቦት ሰባት ልሳን የሆነው ኢሳት ሬዲዮና ቴሌቪዥንን ባለሟል ሲሳይ አጌና በሚሰራበት የሸብር ቡድኑ ጣቢያ ላይ፤ ልክ እንደ መፅሔቱ በተመሳሳይ ሁኔታ የኢትዮጵያን መንግስት የሚያጥላሉ የፕሬስ ቀኖናዎችን ሲዘምር እኔ ራሴ በጆሮዬ ለማዳመጤ እማኝ ነኝ። ሌሎች አብነቶችንም ማከል ይቻላል– ግና ጉዳዩ የአደባባይ ምስጢር ስለሆነ የአንባቢዎቹን ጊዜ መሻማት አልፈልግም። ይሁንና በእኔ እምነት ምንም እንኳን መፅሔቱ በራሱ ጊዜ አስቀድሞ በመከላከል ስልት ያልበላውን ቦታ ለማከክ ቢፈልግም፤ እንዲህ ዓይነቱ “እንደ ወረደ” የአጀንዳ ቅብብሎሽ አካሄድ ተቀባይነት አለው ብዬ አላምንም። ምክንያቱም በሙያው የስነ-ምግባር ደረጃ ማናቸውም የሀገራችን የግል ፕሬሶች ሚዛናዊ ዘገባን ማቅረብ ስለሚጠበቅባቸው ነው።

ስለ ቅንነት እያወራ ነገር ግን ራሱ ውሸትን ጭምር እየተጠቀመ ቅን መሆን የተሳነው መፅሔቱ፤ ከፅሑፌ ውስጥ ቀንጭቦና ያላልኩትንም ጨምሮ “ፀሐፊው አዲስ ጉዳይን በተለይ የግሉን ፕሬስ በደምሳሳው የስነ-ምግባር ደንቦችን አክብረህ ካልሰራህ ጨው ለራስህ ስትል ጣፍጥ የሚለው

ብሂል ተግባራዊ ይሆንብሃል በማለት ዛቻና ማስፈራሪያ አስፍረዋል" እያለም በመፈረጅ ያልተገባ ስብዕናን ሊያላብሰኝ ሞክሯል። ከዚህ በተጨማሪም የአንድ ዜጋን ፅሑፍ ያለ አንዳች ማስረጃ "ሊበሏት ያሰቧትን አሞራ…" እስከ ማለት በመድረስ የሃሳብ ፍጭቱን ወደ ሌላ አቅጣጫ እያዞረ የራሱን ውስጣዊ እምቅ ፍላጎት ማሳኪያ አድርጎ ተጠቅሞበታል።እንደ እውነቱ ከሆነ ግን እኔ "ጨው ለራስህ ስትል ጣፍጥ" የሚለውን ብሂል የተጠቀምኩት የመፅሔቱ ሰውዬ መከራከሪያ ሃሳብ ስላጠራቸውና ይህን ክፍተት ለመሙላት ሆን ብለው ሃቁን ለማጣመም እንደሞከሩት አይደለም። አባባሉን የተጠቀምኩበት መፅሔቱ "መንግስት ሆይ፣ ሺህ ዓመት ንገስ" ላለው የርዕሰ አንቀፅ ፅሑፉ የሰጠሁት ምላሽ ነው—ያለ አንዳች አስረጅ መንግስት "ነፃውን" ፕሬስ እያመነመነ ነው ለሚለው አሉባልታ። እናም የእኔ መከራከሪያ "ነፃ" የተባለው ፕሬስ የተመናመነው ራሱ በፈጠራቸው ግድፈቶቹ እንጂ በመንግስት ምክንያት አይደለም የሚል ነው ። ለምን ቢባል፤ የግል ፕሬሶቹ በገበያው ውስጥ ተነባቢ እንዲሆኑና ከገበያ ውጭ እንዳይሆኑ እጅግ የበዛ ድርሻውን መውሰድ ያለባቸው እነርሱ እንጂ መንግስት ባለመሆኑ ነው። ለነገሩ ከሀገራችን የግል ፕሬስ ታሪክ እንደምንረዳው የግል ሚዲያውን ለጥፋት የዳረጉት አብዛኞዎቹ ባልደረቦቹ ጋዜጠኛ ሳይሆኑ በፖለቲካዊ ስሜት ተገፋፍተው ያለ ሙያቸው ወደ ስራው የተቀላቀሉ በመሆናቸው ነው። አንዳንዶቹም የቀድሞው ስርዓት አባላት እንዲሁም ወታደሮች እንደነበሩ በዕድሜያችን ያየነው ዕውነታ ነው።

እናም ፕሬሱ ሁሌም የጋዜጠኝነት ስነ-ምግባርን እንዲሁም የሀገሪቱን ህግ ሳያከብር ውሸትን ብቻ እያራገበ በመንቀሳቀሱ እንዲሁም አንድን ብሔር ከሌላው ጋር ለማጋጨት መጣሩ ብሎም የሀገሪቱን ህግና ስርዓት ተፃርሮ በመስራቱ በህዝብ ተጠልቶ አብዛኛው አካላቱ ከገበያው ውስጥ በዝረራ ወጥተዋል። እናም ይትብሃሉን የተጠቀምኩት አዲስ ጉዳይ መፅሔትም በህዝብ ተጠልቶ ከገበያው እንዳይወጣ ምክር ለመስጠት መሆኑን ሁሉንም ነገር አጣሞ የሚያየው የዝግጅት ክፍሉ መረዳት ይኖርበታል። አባባሉ ከማስፈራሪያና ከዛቻ ጋር የሚያገናኘው አንዳችም ጉዳይ የለምና። ዳሩ ግን አሁንም ሃቁን ውድ አንባቢዎቼ ይፈርዱኝ ዘንድ ከዚህ አኳያ በፅሑፌ ላይ ያልኩትን ለማስታወስ ያህል ማቅረብ እወዳለሁ።…

> *"…መንግስት የግሉን ሚዲያ እንደምን እንደሚያመነምን ለማንም ግልፅ አይደለም። ምናልባት መፅሔቱ በኪሳራ፣ በህጋዊ የአሰራር ማዕቀፍን በመደፍጠጥ አሊያም ከማተሚያ ቤት ጋር ባላቸው የግል ውል ምክንያት ከገበያው በራሳቸው ጊዜ የወጡትን አንዳንድ የግል ፕሬሶችን ችግር በመንግስት ላይ ለማላከክ ፈልጎ ከሆነ፤ በዚህ ጉዳይ ውስጥ መንግስት እጁን ሊያስገባ አይችልም። ምክንያቱም የፕሬሱን ኪሳራ የመሸፈን፣ ፕሬሱ ህጋዊውን አሰራር እንዲጥስ የማበረታታት ብሎም ከማተሚያ ቤቶች ጋር ችግር ሲኖር አታሚዎች ከፕሬሱ ጋር የገቡትን ውል እንዲቀይሩ የማስገደድ ተግባርም ይሁን ሃላፊነት ስለሌለው ነው። እናም የግል ፕሬሱ እንዲያድግ መንግስት*

*አሁን እያደረገ እንዳለው ሁሉ፣ ለጋዜጠኞች ከለላ የሚሰጥ ህግን የማበጀት፣ አስፈላጊ ስልጠናዎችን የማዘጋጀትና ተመሳሳይ ተግባራትን ከመከወን በዘለለ የሚያደርገው ነገር ያለ አይመስለኝም። እናም የራስን ችግር በመንግስት ላይ ለማላከክ መሞከር አሳፋሪ መሆኑን መፅሔቱ ሊያውቀው ይገባል። በመሆኑም በእኔ እምነት የግሉ ፕሬስ እንዳይመናመን ከተፈለገ ራሱን ነፃና ጤናማ በማድረግ እንዲሁም የራሱን የሥነ-ምግባር ደንቦች አክብሮ መስራት ይኖርበታል። አሊያ ግን "ጨው ለራስህ ስትል ጣፍጥ" የሚለው ብሂል እውነት መሆኑ የሚቀር አይመስለኝም።" …*

እርግጥ እዚህ ፅሑፍ ውስጥ ከምክር ውጪ ማስፈራሪያና ዛቻ በባትሪ እንኳን ተፈልጎም ቢሆን ሊገኝ እንደማይችል ሚዛናዊው አንባቢዬ አይስተውም። የመፅሔቱ ፀሐፊ ያልተጨበጠ ስጋት የወለደው ተራ ጥርጣሬ መሆኑንም ጭምር። እናስ ታዲያ የግለሰቦችን ስም ማጥፋት ምን አመጣው?...የሃሳብ ትግልን በመፍራት "ሊበሏት ያሰቧትን ምንትስ" እያሉ ዜጎች የራሳቸውን እምነት እንዳይገልፁ ያልተገባ ስም መስጠትስ ምን ይሉት ጋዜጠኝነት ይሆን?...

በጥቅሉ ምንም እንኳን መፅሔቱ "ምን ዓይነት ሚዲያ ይበጀናል?" ለሚለው ፅሑፌ በአብዛኛው ምንም ዓይነት ምላሽ አልሰጠም። ለእኔ ይህ ድርጊቱ ምንም ላለት ካለመቻል የመነጨ ነው—ምንም እንኳን ፀሐፊው በሌለ ማንነት ቲዮሪ አጣቅሰን፣ ሰማይን ጠቅሰን ምንትስን ቆርሰን ምላሽ እንሰጥ ነበር ግን…እያሉ ሊያምታቱ ቢፈልጉም። ውድ አንባቢዎቼ ግን በእኛ ሀገር የግል ፕሬስ ውስጥ ያሉት አንዳንድ ጋዜጠኞች ጋዜጠኛ ሳይሆኑ በመንግስት ላይ ያለ አንዳች ጥናትና ማስረጃ ያሻቸውን ይፅፉና ሙያውን ልክ እነ ሲሳይ አጌና እና መሰሎቻቸው እንዳደረጉት የተሻለ ኑሮ ማፈላለጊያ የቪዛ ማስመቻ አድርገው እንደሚጠቀሙበት ልትገነዘቡት ይገባል። ታዲያ የአዲስ ጉዳይም በተለያዩ ጊዜያት 'በዐብይ ጉዳይ' አምዱ ስር የሚያትማቸው ጥናትና ማስረጃ አልቦ እንዲሁም ደፈናዊ ጥላቻን ያነገቡ ዘገባዎች ሀገር ለሚያውቀው ለዚህ 'ታክቲክ' እየዋለ ከሆነ፤ በሀገራችን የግል ፕሬስ ዳግመኛ የማፍርበትና የምሸማቀቅበት ወቅት ያኔ ይሆናል። ቸር እንሰንብት።